INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY

የውስጥመጻጻፊያ

ቁጥር፡ ም/ሥ/የአድ/06/508/08

ቀን ፡ 06/02/2008

- ለ፡ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት
- ለ፡ ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለ፡ ሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት
- ለ፡ መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለ፡ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
- ለ፡ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
- ለ፡ በመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የሥራ ሂደት
- ከ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

የጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት በቁጥር 3.3.1/415/08 ጥቅምት 02 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/78 መስከረም 05 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በመቀሌና በባህርዳር አውሮኘላን ማረፊያዎች በኩል ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ ምርት ውጤቶችን እና ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት የትራንስፖርት ወጪ መንግስት እንዲጋራ የወጣውን የመመሪያ ቁጥር 36/2005 ማሻሻያ የተላከውን 1 ገጽ ደብዳቤ እና 2 ገጽ ኮፒ በአባሪነት አያይዘን የላክን ሲሆን፤ ተገቢው ጥንቃቄ ተወስዶ እንዲፈጸም አሳስባለሁ።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለ፡ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለ፡ ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ም/ሥራ አስኪያጅ
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

Memo AZ - aw

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

ባሉበት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/78 መስከረም 05 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በመቀሌና ባህርዳር አውሮፕላን ማረፊያዎች በኩል ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ሽርብስ ምርት ውጤቶችን እና ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት የትራንስፖርት ወጪ መንግስት እንዲጋራ የወጣውን የመመሪያ ቁጥር 36/2005 ማሻሻያ የላከበትን 1 ገጽ ደብዳቤና የመመሪያውን ማሻሻያ 1 ገጽ አባሪ ለተገቢው አፈፃፀም የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ማርታ ስዩም

የጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ቡድን አስተተባባሪ

ግልባጭ፣

- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት

  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣

25-791
19/01/08

ቀ/8/6/187 76
7/1/08

2/ቀ/2496
2/1/08

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር Ref. No. 7/ፈ/1/2/78
ቀን Date 05/01/2008

ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ
ለኢትዮጵያ አየር መንገድ
ለአበባ፣አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ማህበር
<u>አዲስ አበባ</u>

በመቀሌና ባህርዳር አውሮፕላን ማረፊያዎች በኩል ወደውጭ አገር የሚላኩ የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ ምርት ውጤቶችን እና ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት የትራንስፖርት ወጪ መንግሥት እንዲጋራ የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 36/2005 ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ መዋሉን እና የትራንስፖርት ድጎማው ለ2007 የበጀት ዓመትም እንዲቀጥል መወሰኑ ይታወቃል።

ሆኖም የትራንስፖርት ድጎማው ተለዋጭ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ በመመሪያው ላይ ማሻሻያ ተደርጓል።

ስለዚህ የመመሪያውን ማሻሻያ 1 ገፅ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ
ለትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር</u>

Lett W'GT

## ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማ መመሪያ ቁጥር 36/2005ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

ወደ ውጭ ለሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 36/2005 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያው እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማ መመሪያ ቁጥር 36/2005ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ማሻሻያ**

ወደ ውጭ ለሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የወጣው መመሪያ ቁጥር 36/2005 እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል።

አንቀጽ 7 ተሠርዞ በሚከተለው አንቀጽ 7 ተተክቷል።

"7. ለሆርቲካልቸር ምርቶች ኤክስፖርት የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ ተለዋጭ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በየዓመቱ የሚሰጥ ይሆናል።"

3. **ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ማሻሻያ ከመስከረም 10 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም 5 ቀን 2008 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

ሆርቲካልቸር Dire.W/GT